# “ሥልጣን ምን ያደርጋል፣ሺ ዓመት አንኖር”

## (ዶ/አብይ) ሲነጻጸር አንዳንድ የወያኔ አምባሳደር ሥልጣናቸውን ለማራዘም ባሉበት አካባቢ የምስጉንነት ሰርተፍኬቶች እየጠየቁ ስለመሆናቸው!!

ብርሃንደጅ ሃሰን (01/08/18)

ሰዎች በጣም ከሚመኝዋቸው ነገሮች አንዱ የፖሊቲካ ሥልጣን መጨበጥ ነው ።ትላልቅም ሆኑ ትናንሽ የፖለቲካ ቡድኖችና የፖለቲካ ቡድን መሪዮች ኅልው መሆን ከጀመሩ 8000 ዓመታት ሆኗል። ከይህን ያህል የሰው ልጅ ፖለቲካዊ ታሪክ ጀምሮ -በጠመንጃ አፈሙዝም ሆነ በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን የጨበጡ መሪዮች -በህገ መንግሥት ካልተገደቡ ፣በሕዝብ አመጽ ካልተገፈተሩ ፣ በበሽታና በሞት ካልተሸነፉ በቀር ሥልጣን በቃኝ ፣ሥልጣኔ ተረከቡኝ ያለ መሪ ነበር ብሎ ለመገመት ያስቸግራል ።

(ከእውነተኛ ስብዕና ፣ከብስለት ፣ከመጠቀ ንቃተ-ኅሊና ወዘተ..) ተነስተው ይሁን ወይም ከአንገት በላይ ሰውን ለመማረክ(for captivation) ይበሉት ፣ ሥልጣን ላይ ሁነው ‛ሥልጣን ምን ያደርጋል! ሺ ዓመት አንኖር!” ብሎ የሥልጣን ከቱነት የሰበከ ብቸኛ መሪ ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ ሳይሆኑ አይቀሩም ባይነኝ ።

ይህ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያንና ለሌሎች አሁጉራት የፖለቲካ መሪዮች አዲስ ፡-የፖለቲካ ባህል፣ፍልስፍና ፣ራኢ፣ እይታ ፣ምልከታ ወዘተርፈ አስተምሮት/ዲስኮርስ ነው እላለሁ ። በዚህ አባባላቸው የሚወድዋቸውም የሚጥልዋቸውም መሪዮች እንደሚኖሩ አልጠራጠርም ። ነገር ግን ይህንን በሰማ የሉል/የመልካአ ምድር ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ አድናቆት እንደሚያተርፍላቸው እርግጠኛ ነኝ ። በዚህ አባባላቸው ማኅበራዊ ነጻነታውያን እና ማኅበራዊ ፍትሃውያን (Social Libertarians and Social Justinian’s>ይሽሉሟቸው ይሆናል ።

ከዚህ በተጻራሪ የወያኔዎች ቅጥ ያጣ የሥልጣንና ሃብት የማካበት ጉጉት ስናይ ፤ወያኔዎች ሥልጣንና ሃብት እስከ ከመቃብር ወዲያ የሚፈልጉ ይመስላሉ ። ማለት ሥልጣንና ሃብት ወደ መቃብራቸው ይዘው የሚገቡ ይመስላቸዋል ። ቻይናዎች የሞቱትን ሲቀበሩ በርካት አርቲፊሻል የቻይናዎች ገንዘብ <yuan> አብሯቸው ይቀበራል ። ለዚያ የሚሰጡት ምክንያት ሟቾች ከሞት ወዲያ ባለው ዓልም ድሃ እንዳይሆኑ ነው ይላሉ ፤ ወያኔዎችም እንደዚያ የሚያስቡ ይመስለኛል ።

አንዳንድ የወያኔ አምባሳደሮች ሥልጣናቸውን ለማራዝም ወይም ከሥልጣናቸው ላለመውረድ በተሾሙበት አካባቢ በሥልጣናቸው ተጠቃሚ ከሆኑ ቡድኖች -‛ምስጉን ፣ትጉህ፣ብቁ’ ወዘተርፈ የተሰኙ የድጋፍና የሽልማት ሰርተፍኬት ማሰባሰብ ጀምሯል።

ከእነዚህም አንድዋ በአውስትራሊያ የኢትዮጵያ አምባሳደር የሆነችው ትርፋ ኪዳኔ ናት። እንዴት ? ከተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አውስትራሊያ የፈለሱትን ኤሊት ነን ባዮች በሚኖሩበት አገር የእኔ ነው ለሚሉት ማኅበረሰብ/ኮምኒቲ ምንም አስተዋጾ ሳያደርጉ ፣ብዙሃን አፍሪካኖችን ለመጥቀም ሳይሆን ከመንግሥት የገንዘብ እርዳታ/ፈንድ አግኝተው ራሳቸውን ለመጥቀምና ለመሸላለም ያቋቋሟቸው ፡-የአፍሪካ ተንታኝ ፣የአፍሪካ ቀን ፣የፍሪካውያን ማኅበር መሪዮች/መሪነት መድረክ ፣የአፍሪካውያን ማኅበረሰብ ማኅበር በካንቤራ (African Think Tank,African

day,Celebration of African day, African Communities Leadership Forum, African Community Association in ACT) የተባሉ ድርጅቶች አሉ። ብዙ ባይሆኑም የወያኔ ቤተሰብ የሆኑ፣ ወያኔን ሲያጅቡና ሲያገለግሉ የኖሩ ጥቂት የእነዚህን ድርጅቶች አባል የሆኑ ኢትዮጵያውያን አሉ ። ከነሱም አንዱ የአቦይ ስብሃት ወንድም አቢሶሎም ነጋ ነው ። የድጋፍና የሽልማት ሰርተፍኬቶች የሚሰጡት በትርፉ ኪዳኔ በይፋ ወይም በቀጥታ ጠያቂነት ሳይሆን ፣ በእጅ አዙር በወያኔዎች ቤተሰቦች ፣ጭፍሮቻቸው እና ከላይ እንደጠቀስኩት በሥልጣኗ ተጠቃሚዮችን አነሳሽነት/ኢኒ ሼትቭ ነው ።

"ምርጥ አፍሪካዊት አምባሳደር በአውስትራሊያ <the best African Ambassador in Australia>" በሚል እ.ኤ.አ አቆጣጠር በሴፕቴምበር 22/09/18 ሊሸልማት የተዘጋጀው (የአፍሪካውያን ማኅበረስብ ማኅበር (African Community Association in Australian Capital Territory/ACT) የተሰኘ ድርጅት ነው።ሌሎችም ይቀጥሉ ይሆናል ፡፡

ተከለሰውነትዋ ከፍ ለማድረግ በካንቤራ ታይም መጽሄት <Canberra Time Magazine> እንድትወጣ ሳያደርጉ አይቀሩም ተብሎም ይገመታል ።

ትርፉ ኪዳኔ እ.ኤ.አ በጁላይ 3/ 2018 በስቢስ <SBS> ሬዲዮ ቃለመጠይቅ የሰጠችው መልስ ቀድሞ ከሰጠቻቸው መልሶች በይዘትም በቅርጽም እጅግ በጣም የተለየ ነው ። ከዚህ ቀደም ስለወያኔ ተቀናቃኞች ስትጠየቅ ፤ በንቀት ፣በስድብ ፣በፉከራ ወዘተ..ነበር መልስ የምትሰጠው ። የዛሬ ሁለት ዓመት በሃምሌና በነሃሴ ወራት ፣ በጎንድርና በባህርዳር የተደረገውን ሕዝባዊ አመጽ ለማቀብ/ለመገደብ የዘመተው የአጋዚ ጦር በባህርዳር ብቻ ከ 50 በላይ ወጣቶች መግደላቸው እንደትላንት እናስታውሰዋለን ።

እ.ኤ.አ 5 Sept 2016 ትርፉ ኪዳኔ ስለሕዝባዊው አመጽ ለዚሁ ለ<SBS> ሬዲዮ ቃለመጠይቅ ቀርባ ፤ "ፀረ-ኢህአደግ የሕዝብ እንቅስቃሴ የለም ፣አሁን ያለው ሥርዓት የሚጠላ የለም፣ የሚያስቸግሩት የ 13 ዓምት ሕጻናት ናቸው፣መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን መውሰድ የሚችል ተቃዋሚ የለም፣በወሬና በሚዲያ መንግሥት አይገለበጥም ፣አሁን ያለው የፌደራል ሥርዓት አፍርሶ በአንድ እጠቀልላሁ የሚል ከመጣ አገር ይፈርሳል፣በዘረኝነት ማንም አያሸንፍም፣ትርፉ መጨፋጨፍ ይሆናል ፣አደጋው ከተጀመረ እርስ በርስ መበላላት ፣መጠፋፋትና መበታተን ይሆናል" ወዘተርፈ ነበር ያለችው ። በዚያ ቃለመጠይቅ የሰጠችው ሃሳብ እርስ በራሱ የሚጋጭ/የሚላተም ቢሆንም ፤ ሕዝባዊ ቅሬታው የኢህአደግ መንግሥትና የፌደራሉ ሥርዓት ከመጥላት ሳይሆን ከዘረኝነት/ትግሬ ከመጥላትና ትግሬ ለምን ይገዛናል ከማለትነው ። ስለሆነም እንጨፋጨፋለን እንጂ ሥልጣን አንለቅም ፤ አገሪቷም እኛ ካልገዛናት ትበታተናለች ነበር ያለችው ። አንዳችም አስታራቂ/አቀራራቢ ሃሳብ አላቀረበችም ። አባይ ፀሃይ <አባይ ጨለማ> በወቅቱ ያለውን ነው የደገመችው ማለት 'ወያኔ ከሌለ ይህች አገር ትበታተናለች' ያለውን ነበር የደገመቹ ።

https://www.youtube.com/watch?v=88c99cXW_fMhttps://www.youtube.com/watch?v=88c99cXW_fM

እ.ኤ.አ ጁላይ 3/2018 ለዚሁ ለስቢስ <SBS> ሬዲዮ ለውጡና የዶ/አቢን አመራርን አስመልክቶ ለተደረገላት ቃለመጠየቅ የሰጠችው መልስ ከድቀምው በ 180 ድግሪ የታጠፈ ነው ።'አቢይ የወሰዳቸው እርምጃዎች ጥሩ ናቸው ፣ ሰው ሰላም አግኝቷል፣ ሰው አፊይታ አግኝቷል ፣ለውጥ በትግራይም ይመጣል ፣ለውጡን ተቀብላ ከለውጡ ጎን እንድምትሰለፍ ፣የአቢይን አመራር ያለቅድመ ሁኔታ እንደምትቀበል' ወዘተ.. ገልጻለች። በህወሃት መካከል መከፋፈል መኖሩንም ጦቁማለች። ባጭሩ በወያኔ ሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ 'አፎይታና ሰላም እንዳልነበረው ፣ለውጥ እንደምያስፈልገው መስክራለች' ። በአውስትራሊያ ያሉ ትግሬዎች ከላይ በተጠቀሰው ቀን በሰጠችው የቃለመጥይቅ መልሶቿ ስላተደሰቱ ፤ አኩርፏታል እየተባለ ይወራል ።

https://www.sbs.com.au/yourlanguage/amharic/en/audiotrack/its-time-

ወይዘሮ ትርፉ ብልጥ ፖለቲከኛ ናት ፣

<1> "ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ትርፉ ለመላላጥ" መሆኑን ተረታለች

<2> "ወደሽነው ቆማጢት ንጉሥ ምትመሪቂ" እንደሚባለው የሥልጣን ዕድሜዋ ለማራዘም ለአዲሱ አለቃዋ ጸጥ ለጥ ማለት አለባት።

ያም ሆነ ይህ ወይዘሮ ትርፉ የያዘችውን ሥልጣን የምታጣው መስሎ ከታያት የአው- ስትራሊያ ጥገኝነት <አሳየለም> ትጠይቃለች እንጂ ወደ ኢትዮጵያ የምትመለስ አይመስለኝ ም ። ምክንያቱም ከኢትዮጵያ ተዘርፎ በአውስትራሊያ፤በልጆችዋ ስም ያካበተችው ሃብት አላትና ።